Edward Everett Hale:
I am only one,
But still I am one.
I cannot do everything,
But still I can do something.
And because I cannot do everything
I will not refuse to do
The something that I can do.

## ተረግጠህ ተገዛ፣ ወይ፣ ክንድህን አንሳ!!

ሰምቶ ዝም፣
አይቶ ዝም፣
በሆድ ያለ አይነቅዝም፣
ሲሉህ  አብረህ አታዝግም፣
እያስተኙህ  ነው በህልም፡፡
    አዎን ማለት መረታት፣
    አለመመከት መመታት፣
    እንዳሉት አበው በመጻፍት፣
    ከጓዶችህ ጋር ሰነባብት፣
    ምከር በጋራ በቀናት፣
    በህገ አራዊት፣ሥርዓት፣
    ላለመዳኘት በህወሃት፣
    ክንድህን አንሳ በሰዓታት፣
    ጊዜ አትስጣቸው ሳምንታት፡፡
አሊያ…ወይ ..ለራስህ ስትል ታገል፣
ወይ ተረገጥህ እንደ ወደል አህያ ዝምበል፣
አታሳድፍ ወኔያቸውን፣ መንፈሳቸውን  አትበክል፣
ይልቅስ ለራስህ አልቅስ፣ በቁምህ አብላ ተዝካርክን፣
ከገዳይህ ጋር ብላ፣ የሚሊኒዬም ዘካህን፣
በቃሊቲ ጀግኖች ላይ ዳሌህን አሳይ ደንደስክን፣
ውሻ ወደ ትፋቱ ነው፣ በግላጭ እሚሳይ ነውሩን፡፡

እንግዳ ታደሰ/ ኖርዌ.

መታሰቢያነቷ፣ በህገ አራዊት ለተዳኙት መሪዎቻችን፡፡